# የአስመራው ቡድን አስገራሚ ምስጢራዊ ስብሰባ

ዘአማን በላይ

bzaman@yahoo.com

…አስመራ ከተማ፤ታህሳስ 29 ቀን 2005 ዓ.ም። ልክ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ። የቀጣናው አሸባሪዎችና ፀረ-ሰላም ሃይሎች እየተፈለፈሉ ወደ አጎራባች ሀገራት በሚሰማሩበት በሀገሪቱ የደህንነት ቢሮ ውስጥ። በቅፅል ስማቸው "ተኽለ ማንጁስ" እየተባሉ የሚጠሩት የኢትዮጵያ አሸባሪዎችና ፀረ-ሰላም ሃይሎች አስተባባሪ ብርጋዲየር ጄኔራል ተኽለ ክፍላይ እና የኤርትራው የውጭ ደህንነት ኃላፊ ብርጋዲየር ጄኔራል ስምየን ገብረድንግል ጎን ለጎን ተሰይመዋል– ሁለት መቶ የሻዕቢያ የደህንነት ሰራተኞችን ፊት ለፊታቸው ሰብስበው።

አንድ ሰውዬም እንደ ተራ የደህንነት ሰራተኛ ተቆጥረው በሚመስል መልኩ የዚህ ምስጢራዊ ስብሰባ ተካፋይ ናቸው። እኚህ ሰው ለይስሙላ የሀገሪቱ ዋነኛው የደህንነት ኃላፊ ናቸው – ብርጋዲየር ጄኔራል አብርሃ ካሳ። ምንም እንኳን ብርጋዲየር ጄኔራል አብርሃ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸውና ምስጢራዊ ስብሰባውንም መምራት ያለባቸው እርሳቸው ቢሆኑም፤ በአቶ ኢሳያስ "በስውር ከፋፍለህ ግዛው" የአገዛዝ ዘዴ ከተራ አባሎቻቸው ጋር አብረው ተቀምጠው በስብሰባው ላይ የሚወራውን የሻዕቢያውያንን አስገራሚ ልፈፋ እንደ እንግዳ በአድማጭነት እየሰሙነው።…

ይህ አባባል የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ አይደለም። "ኣሰና ዶት ኮም" የተሰኘ ድረ-ገፅ ሰሞኑን ምንጮቹን ጠቅሶ ያስነበበን የትግርኛ ዘገባ እንጂ። እናም በዘገባው የተጠቀሰው ምስጢራዊ ስብሰባ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደርን ማንነት ፍንትው አድርጎ የሚያሳዩ መግለጫዎችን የያዘ በመሆኑ፤ ለውድ አንባቢዎቼ ግንዛቤ ስለሚረዳ በመጠኑም ቢሆን ላቀርበው ወደድኩ። እርግጥም ይህ ስብሰባ የኤርትራ መንግስት እስካሁን ድረስ ይክድ የነበረውን ዕውነታ በራሱ ዋነኛ ታማኝ የደህንነት ባለስልጣናት አማካኝነት ማመኑን የሚያመለክት በመሆኑ፤ ለዚህ ፅሑፍ አንባቢ አስገራሚ ከመሆኑም ባሻገር፤ ዓለም ያወቀውን የአቶ ኢሳያስ መንግስት እኩይ ሴራን እንደ ቢጋ ሰማይ ጥርት ብሎ እንዲያየው ስለሚያደርግ ሃቁን መዳሰስ ተገቢ ነው።

ቀደም ሲል በጠቀስኳቸው ሁለቱ ብ/ጄኔራሎች አማካኝነት የተካሄደው ይህ ምስጢራዊ ስብሰባ ሰባት ያህል የመግለጫ ነጥቦች ቢኖሩትም፤ ከሶስቱ ብቻ ተነስተን የአቶ ኢሳያስን መንግስት እውነተኛ ፀያፍ ተግባራትን ለመረዳት አይከብድም። ይሁንና ነጥቦቹን በመግለፅ ሃቁን

ከመዳሰሳችን በፊት "አቶ ኢሳያስ በማዕረግ ከብርጋዲየር ጄኔራሎቹ የሚልቁት ሜጄር ጄኔራሎች እያሉ ለምን የበታቾችን የየስብሰባው ኃላፊ አድርገው ይልካሉ?" የሚል ጥያቄ ማንሳት የተነሳሁበትን ጉዳይ ይበልጥ ስለሚያፍታታ በመጀመሪያ ወደ ጥያቄው ምላሽ ማቅናት ጠቃሚ ነው።

መቼም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ ላለፉት 21 ዓመታት የአስመራው አስተዳደር በራሱ መዝገበ-ቃላት ውስጥ ያስተዋወቀንን "ኢሳያሲዝም" የተባለ በአቶ ኢሳያስ ስውር ክትትል የሰየመውን ቃል ይዘነጋዋል ብዬ አልገምትም። ግና ከዘነጋው እኔ እንዲህ አስታውሰዋለሁ።...አዎ! "ኢሳያሲዝም" እንዲህ ይላል። ... "ከራስህ ውጭ ማንንም አትመን፣ በየቦታው ላንተ ብቻ ታዛዥ የሆነ ስውር ሰው ፍጠር" ...እርግጥም ይህ አባባል የ"ኢሳያሲዝም" ዋነኛው መርህ ነው፡፡ ነገሩን ቀለል ባለ አማርኛ ስንተረጉመው "ሰውን ማመን ቀብሮ ነው" አለች ቀበሮ የማለት ያህል መሆኑ ነው፡፡

እናም የዚህ መርህ የበላይ ጠባቂ የሆኑት አቶ ኢሳያስ፣ የፓርቲውን ጽህፈት ቤት፣ የጦር ኃይሉንና የደህንነት መዋቅሩን ላሻቸው ጉዳይ እንደየጊዜውና እንደየሁኔታው በከፍተኛ ጥርጣሬ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ከእያንዳንዱ ሚኒስትር፣ ጄኔራልና የደህንነት ሰራተኛ ጀርባም "ስውር ተከታታዮችን" በመመደብ ዕለታዊ ውሎአቸውን በዓይነ ቁራኛ ይከታተላሉ፡፡

ይህ ብቻ አይደለም- በአቶ ኢሳያስ አምባገነናዊ መንግስት መዋቅር ውስጥ አስፈሪዎችና "ጥላቸው የሚከብድ" የሚባሉ የሰውዬው የቀኝ እጅ ግለሰቦች አሉ፡፡ ከእነዚህ የቁርጥ ቀን ሰዎች ውስጥ ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው ሁለቱ ጄኔራሎች በተጨማሪ፣ ብ/ጄኔራል ኢዩብ (ሐሊባይ)፣ ብ/ጄኔራል ተመስገን በርሀ (ወዲ በርሀ)፣ ብጄኔራል ዘርኢት ወለማርያም፣ ብ/ጄኔራል ፍፁም (ወዲ መምህር) እና ብ/ጄኔራል ሓዱሽ ኤፍሬም ተጠቃሽ ናቸው።

የ"ኢሳያሲዝም" ዋነኛ ተዋናዮች ናቸው ተብለው እምነት የሚጣልባቸው እነዚህ ጄኔራሎች፣ እንደ ወታደር የዕዝ ሰንሰለት ሥነ-ሥርዓት የሚባል ነገርን የሚያውቁ አይደሉም፡፡ በማንኛውም ሚኒስቴር መስሪያ ቤትም ይሁን በዞን አመራርነት አሰራር ውስጥ ጣልቃ ገብተው ያሻቸውን ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡

ውሳኔያቸው ትክክል ይሁንም አይሁን ጄኔራሎቹ ግን ሁልጊዜም 'ትክክል ናቸው' ተብሎ ይታሰባል - "ንጉስ አይከሰስ፣ ሰማይ አይታረስ" እንዲሉ አበው፡፡...ዳሩ ግን ምን ያደርጋል?!...አቶ ኢሳያስ የራሳቸውን ኮቴ እንኳን የማያምኑ ግለሰብ በመሆናቸው፣ በእነዚህ ጄኔራሎች ላይ "ጄኔራል ያልሆኑ ጄኔራሎችን"ን በመመደብ ጭምር በሚሰሩት ስራ ራሳቸውን እንዲጠራጠሩ ያደርጓቸዋል፣ በነገር ይጠላልፏቸዋል፣ አንዱ በሌላው ላይ ቂም እንዲይዝ ያደርጋሉ፡፡...

…የኤርትራን ወታደራዊ መዋቅር በቅርበት የሚከታተሉት ወገኖች እንደሚገልጹት፣ በ"ኢሳያሲዝም" የ"ታማኝነት" መዝገብ ውስጥ ከተካተቱት ጄኔራሎች መካከል፣የሀገሪቱ አየር ኃይል ዋና አዛዥና የኤርትራ ወጣቶች ጉልበት የሚበዘበዝበት የ"ዋርሳይ ይካኣሎ" ዘመቻ ሊቀመንበር ሜጀር ጄኔራል ተክላይ ሃብተስላሴ ዋነኛው ናቸው፡፡

እኚህ ጄኔራል ሌሎች ጄኔራሎችን በንቀት ዓይን የሚመለከቱና ከበርካታ ወታደራዊ አዛዦች ጋርም የማይስማሙ ናቸው፡፡ ይሁንና የ"ኢሳያሲዝም" መንፈስ ቀንደኛ አቀንቃኝ በመሆናቸው ምክንያት የአቶ ኢሳያስ የቅርብ ሰው ለመሆን የቻሉ እንደሆኑ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የዞን ወታደራዊ ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ እስከመሆን ድረስ ስልጣን ያገኙ ግለሰብ ናቸው፡፡

በአንፃሩ ደግሞ አንዳንድ ከፍተኛ ወታደራዊ ባለስልጣናት በጥርጣሬ ይታያሉ (ውድ አንባቢዎቼ በመግቢያዬ ላይ የገለፅኳቸውንና ከተራ የደህንነት አባላት ጋር እንደ ተጋባዥ እንግዳ የራሳቸውን መስሪያ ቤት መግለጫ ቁጭ ብለው ያዳምጡ የነበሩትን ብርጋዲየር ጄኔራል ኣብርሃ ካሳን ያስታውሷል!)። እናም ማንንም የማያምነው ይህ የ"ኢሳያሲዝም" መንፈስ፣ በጦር ኃይሉ ውስጥም ቢሆን ጄኔራሎቹን "ታማኝ"ና "ታማኝ ያልሆነ" እያለ በመከፋፈል እንዲሁም አንዱ ሌላውን እንዲጠራጠር አድርጎ ነው መዋቅሩን ያደራጀው፡፡ በመንፈሱ የበላይ ተቆጣጣሪ አቶ ኢሳያስ የሚመራው የ"እርስ በእርሱ አናክሰው" ቡድን፣ የመከላከያ ሚኒስትሩን ጄኔራል ስብሃት ኤፍሬምንና ሌሎች ነባር ጄኔራሎችን ገሸሽ ያደረገና በ"ታማኝነት" ያልመዘገበ መሆኑም ይነገርለታል፡፡

ይህን እውነታም በኤርትራ ጉዳዮች ላይ በርካታ ምርምሮችን ያካሄደው ዳን ኮኔል የተባለ ተመራማሪ አረጋግጧል፡፡ የመከላከያ ሚኒስትሩ መገለል የቆየ መሆኑን አስመልክቶም፣ "…ጄኔራል ስብሃት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ ምንም ዓይነት ሚና እንደሌላቸው በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ወቅት ታይቷል" በማለት ነበር የገለጸው። አዎ! እርግጥ ጄኔራሉ በአቶ ኢሳያስ ትዕዛዝ በጎረቤት ሀገሮች ጣልቃ ለሚገቡ አሸባሪዎች ስትራቴጂና ታክቲክ ይንደፉ እንጂ፣ ይህ ነው የሚባል ውሳኔ የመስጠት ስልጣን እንደሌላቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡…

እርግጥ የአቶ ኢሳያስን ስውር መረብ ያጠናው ዳን ኮኔል በዚህ ብቻ አያበቃም።… ምንም እንኳን ዳን ኮኔል በአንድ ወቅት የኢሳያስ አፈ-ወርቂ አድናቂ የነበረ ቢሆንም፣ ኤርትራን አስመልክቶ ባደረጋቸው ጥናቶች አንቱታን ማትረፍ የቻለ ሰው ነው፡፡ በአሜሪካ ቦስተን ውስጥ የጋዜጠኝነት መምህሩና ተመራማሪው ዳን ኮኔል፣ በምርምሮቹ ወቅት ቀደም ሲል ለአቶ ኢሳያስ የነበረው አድናቆት እየከሰመ ሄዶ፣ የማታ ማታ ወደ ሃዘንነት ተቀይሯል፡፡ እናም ነገሩ "ሲያልቅ አያምር" እንዲሉ ነውና የአቶ ኢሳያስን የአንድ ሰው መንግስታዊ አወቃቀርን "መውጫ የሌለው የወፍ ጎጆ" ሲል ይመስለዋል፡፡ ለመሆኑ ዳን ኮኔል ይህን ሲል ምን ማለቱ ይሆን?…

…እንደ ተመራማሪው ዳን ኮኔል የአንድ ወቅት ገለጻ፣ አቶ ኢሳያስ ጥላቸውን የማያምኑ ተጠራጣሪ ሰው ናቸው፡፡ ይህ የመጠራጠር አባዜያቸውም፣ ነገሮችን በዲፕሎማሲያዊ ውይይት ከመፍታት ይልቅ፣ ወታደራዊ ፍጥጫ እና ጦር መምዘዝ መፍትሄ እንዲመስላቸው አድርጓል፡፡ ሰውዬው ማንንም ስለማያምኑ፣ የሚፈልጉትን ነገር ዓላማና ግብ ለብቻቸው በመወሰን ለአጫፋሪዎቻቸው በትዕዛዝ መልክ ያስተላልፉታል፡፡ በሀገረ-ኤርትራ ህጉም፣ ሸንጎውም፣ የውጭ ጉዳዩም ይሁን የሀገሪቱ መንግስት ተግባራት በአንድ ግለሰብ እምነትና ፍላጎት የተቃኘ ነው፡፡

የሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩትና በአሁኑ ወቅት በድብደባ ምክንያት ሁለቱም ዓይኖቻቸው ታውረው ኢራ-ኢሮ እስር ቤት እየማቀቁ የሚገኙት አቶ ጴጥሮስ ሰለሞን በአንድ ወቅት ለዳን ኮኔል እንደነገሩት፣ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ እ.ኤ.አ በ1994 ከሱዳን ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ሲያቋርጡና በቀጣዩ ዓመትም የመንን ሲወርሩ እርሳቸው የሚያውቁት አንዳችም ነገር አልነበረም፡፡…

በጥቅሉ ስውሩ መንፈስ "ኢሳያሲዝም" የቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት ታራምደው እንደነበረው የ"ማርክሲዝም ሌኒንዝም" የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም አይደለም – የአንድ ግለሰብ እምነትና አስደንጋጭ ጥላ እንጂ፡፡ "ኢሳያሲዝምን" ዓለም እንደከሰመው "ማርክሲዝም ሌኒንዝም" በገሃድ ባያውቀውም፣ በኤርትራው ፖለቲካዊ -ኢኮኖሚ መንግስታዊ መዋቅር ውስጥ ግን በአካል በኢሳያስ አፈወርቂነት የሚገለጽ ሲሆን፣ በመንፈስ ደግሞ ጠብ-መንጃውን በስውር አቀባብሎና ካራውን ስሎ መዋቅሮችን የሚቆጣጠር ኃይል ነው፡፡

ይህ ኃይል በአካል የአቶ ኢሳያስ አፈወርቂን ጭንቅላትና ጭንቀትን እያነበበ ሲሰራ፣ በመንፈስ ደግሞ የአቶ ኢሳያስን ስውር የክትትል ሰይፍ በመፍራት አንገቱን ቀብሮ የሚኖር ቡድን ነው፡፡ እናም ቡድኑ በሁሉም መንግስታዊ መዋቅሮች ውስጥ እንደሚንቀሳቀስ ልብ ይሏል።…ታዲያ ከዚህ በመነሳት ሁለቱ ብ/ጄኔራሎች በኤርትራ መከላከያ ውሰጥ ያሉ የአቶ ኢሳያስ ስውር መረብ ተቆጣጣሪዎች መሆናቸውን ለመገንዘብ የግድ የስብሰባው ተካፋይ መሆንን አይጠይቅም– ምንም እንኳን ራሳቸውም ቢሆኑ ስውር ተከታታይ ያለባቸው መሆኑ የማይታበይ ሃቅ ቢሆንም። …ስለሆነም ውድ አንቢዎቼ አቶ ኢሳያስ ለምን "ታላላቆች" እያሉ "ታናናሽ" ባለስልጣናትን እንደሚጠቀሙባቸው ግንዛቤ መያዛችሁን በመተማመን፣ ወደ ተነሳሁበት የመግለጫዎቹ ነጥቦች ላምራ።

ለመሆኑ በእነዚህ ሁለት የአቶ ኢሳያስ ስውር ሰይፈኞች የተነሱት ሶስቱ የመግለጫ ነጥቦች ምንድናቸው?–አዎ! ነጥቦቹ እንዲህ የሚነበቡ ናቸው።…የመጀመሪያው "የኢትዮጵያን መንግስት እኛ ወደ ምንፈልገው አቅጣጫ እንዲዞር አድርገነዋል። ለአብነት ያህል ሶማሊያ ገብቶ አል-ሸባብን እንዲያስስ በማድረግ አቅጣጫውን አስተነዋል። ውጤቱም ከመለስ ሞት በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ

በግልፅ ታይቷል። በዚህ ዘዴም ለሰባት ዓመታት ያህል በአል-ሸባብ አማካኝነት ተጠቅመንበታል። አሁን ደግሞ ይህ ችግር በኢትዮጵያ ውስጥ በፈጠርነው አል-ሸባብ አማኝነት በገሃድ እየታየ ነው። በኢትዮጵያ መስጊዶች ውስጥ እየታየ ያለው እስላማዊ እንቅስቃሴ የጥረታችን ውጤት ነው" ይላል።

ሁለተኛው መግለጫ መሳይ ዲስኩርም "የፈለግነውን ነገር ስላደረግን ከአሁን በኋላ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ጦርነት ማካሄድ አያዋጣንም፤ አያስፈልገንም" በሚል የቀረበ ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ "በሠራዊታችን ውስጥ ያለውን ማጉረምረምና ሃሜትን ፀጥ ለማሰኘት ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ የሆነ የሠራዊት አባላት ይቋቋማሉ። እነዚህ አባላትም ወደ ውጭ እንዳይኮበልሉ ከፍተኛ ቁጥጥር እናደርጋለን" የሚል ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ ሶስት ነጥቦች እንኳንስ ለሌላው ሰው ቀርቶ ለተናጋሪዎቹ የአቶ ኢሳያስ ተላላኪዎችም ቢሆን ግልፅ አይደሉም–ለምን ቢባል፣ ራሳቸውን በራሳቸው ካጋለጡበት የመጀመሪያው ነጥብ በስተቀር ሌሎቹ የተለመደው የሻዕቢያ ውሸትና አምባገነንነት መገለጫ ብቻ በመሆናቸው ነው። እንዲያውም አቶ ኢሳያስ ከገቡበት ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ አጣብቂኝ ውስጥ ያወጣኛል በማለት የስልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም የተጠቀሙበት እንጭጭና ግብ የሌለው ፕሮፖጋንዳ ነው ማለት ይቻላል።

ለማንኛውም እስቲ የመጀመሪያውን ነጥብ ዕውነታ እንመርምር። በመጀመሪያ ደረጃ ሻዕቢያ እንዳለው የኢትዮጵያ መንግስት ሰራዊቱን ወደ ሶማሊያ ያስገባው በመፍረክረክ ላይ የሚገኘውና ለራሱ አቅጣጫው የጠፋበት የኤርትራ መንግስት በራሱ ዓለም ውስጥ እራሱን በማንቆለጳጰስ እንደሚያወራው የተራቀቀ መንግስት ሆኖ ሀገራችንን አቅጣጫ ስላሳታት አይደለም። ይልቁንም በወቅቱ በቅድሚያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች፣ ኋላ ላይም አል-ሸባብ በሀገራችን ላይ ከደቀኑት ግልፅና ድርስ አደጋ (Clear & present danger) በመነሳት መንግስታችን ሀገርን የመከላከል ተግባር ነው የከወነው።

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ የማይዘነጋ ሃቅ አለ። ይኸውም የኤርትራ መንግስት አሸባሪዎቹን ከማሰልጠን ባለፈ በድንበር እንኳን የማይገናኛት ሶማሊያ ውስጥ ወታደሮቹን ከአሸባሪዎቹ ጋር አሰልፎ ማዋጋቱ ነው። ይሁንና በመከላከያ ሰራዊታችን ፈርጣማ ክንዶች ከነሽብር ቡድኖቹ አከርካሪው ተሰባብሮ ወደ መጣበት ቦታ እንዲመለስ ተደርጓል። እውነት እውነቱን እንነጋገር ከተባለ የአስመራው ቡድን በምስጢራዊው ስብሰባ ላይ ማውራት ያለበት ይህን ቅሌቱን እንጂ፤ በሌለ ማንነቱ "ኢትዮጵያን እንዲህ አደረግናት" የሚል የፈጠራ ድርሰት አልነበረም።

የኤርትራው የስለላ ቡደን ላመሉም ቢሆን የጠቀሰው ዕውነት አለ። እርሱም "…ለሰባት ዓመታት ያህል በአል-ሸባብ አማካኝነት ተጠቅመንበታል። አሁን ደግሞ ይህ ችግር በኢትዮጵያ

ውስጥ በፈጠርነው አል-ሸባብ አማኝነት በገሃድ እየታየ ነው። በኢትዮጵያ መስጊዶች ውስጥ እየታየ ያለው እስላማዊ እንቅስቃሴ የጥረታችን ውጤት ነው" የሚል ነው። እርግጥም የአስመራው ቡድን አውቆም ይሁን ሳያውቅ የአል-ሸባብ የቅርብ አጋርና ስምሪት ሰጪ ብሎም ሀገራችን ውስጥ በሃይማኖት ሽፋን የሚከናወኑ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን እየመራ መሆኑን በራሱ ጊዜ ጭንቅ ሲይዘው አምኗል።

ይህ የማያወላዳ የሻዕቢያውያን ምስጢራዊ እማኝነት እርግጥም ሀገራችን ውስጥ የሃይማኖት ችግር የሌለ መሆኑን የሚያመላክት ነው። አዎ! ሀገራችን ውስጥ ያለው ዕውነታ ማንኛውም ሃይማኖት ህገ-መንግስታዊ ዋስትና የተሰጠው በመሆኑ፤ በእስልምናም ይሁን በክርስትና ሃይማኖቶች ውስጥ ተቻችሎ መኖርና መከባበር ብቻ ነው ያለው። ነገር ግን በሃይማኖት ሽፋን እንደ ኤርትራ መንግስትና ተላላኪው አል-ሸባብ ያሉ የራሳቸው የሽብር ዓላማ ያላቸው ሃይሎች ሀገራችን ውስጥ አክራሪዎችን አስርገው ለማስገባት በመሞከር ሁከትን ለመፍጠር ይሻሉ። ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ይህ ተግባራቸው በመምከን ላይ ቢሆንም። እናም ሻዕቢያ እንደሚደሰኩረው በዚህ ረገድም ያከናወናቸው እኩይ ሴራዎች በህዝብና በፀጥታ ሃይሎች ትብብር ሊሰምርለት ያልቻለ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

እርግጥ ባለፉት ጊዜያት ሀገራችን ፣ ኢጋድ፣ አፍሪካ ህብረትና በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት በተደጋጋሚ የኤርትራ መንግስት ቀጣናውን ከማተረማመስ እንዲቆጠብ እንዲሁም አል-ሸባብ ለሚሰኘው የሽብር ቡድን የሚያደርገውን ቀጥተኛ ድጋፍ እንዲያቆም ቢጠየቅ አሻፈረኝ ማለቱ ይታወሳል። እናም ዛሬ ላይ የአገዛዝ ዕድሜውን ለማራዘም ሲል ትናንት የተጣለበትን በተመድ የቀጥታው ምክር ቤት የኤርትራና የሶማሊያ ጉዳይ አጣሪ ቡድን ሪፖርት አማካኝነት የተጣለበትን ሁለት ማዕቀቦችን ትክክለኛነት አምኗል ማለት ይቻላል–ቢያንስ በምስጢራዊ ስብሰባው።

ታዲያ እዚህ ላይ የፀጥታው ምክር ቤት አጣሪ ቡድን ሪፖርት በአል-ሸባብና በኤርትራ መንግስት መካከል ያለውን ቁርኝት ማውሳት ጉዳዩን በውል ለመረዳት ያግዛል። እናም ወደ ኋላ መለስ ብለን እንዲህ እንመለከተዋለን።… የኤርትራ መንግስት አል - ሸባብን ጨምሮ በርካታ ሽብርተኛ ቡድኖችን "በፈታውራሪነት" ከመምራቱም በላይ፤ ቋሚ የገንዘብና የህገ - ወጥ ጦር መሣሪያዎች ምንጭ ሆኖም አገልግሏል፡፡ ከዚህ ባሻገርም በአዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረትን 16ኛው የመሪዎች ልዩ ጉባዔን ለማደናቀፍ፤ ትክክለኛው የሽብር ቡድን የትኛው እንደሆነ እስከምንቸገር ድረስ የሚያምታታውን የ"ኦነግ" ቅጥረኞችን በመላክ ለማሸበር ያደረገው ሙከራ ሁነኛ አስረጅ መሆኑን የፀጥታው ምክር ቤት ተገንዝቧል፡፡

ላለፉት 20 ዓመታት በእርስ በርስ ጦርነት በምትታመሰው በዚያች ሀገር ውስጥ ዘልቆ በመግባት በእሳት ላይ ነዳጅ የማርከፍከፍ አሉታዊ ሚናውን ሲወጣ ቆይቷል፡፡ የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) አባል ሀገራት ጉዳዩን ለፀጥታው ምክር ቤት "አቤት" ማለታቸው ትክክለኛ እና አግባብነት ያለው መሆኑን የተረዳው የፀጥታው ምክር ቤት፤ በአስመራው የሽብር ቡድን ላይ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በአጣሪ ቡድኑ ከቀረቡት ሃቆች ተረድቷል፡፡

ከዚህ ዕውነታ ተነስቶም ታህሣሥ 10 ቀን 2002 ዓ.ም በኤርትራ መንግስት ላይ የጦር መሣሪያ ማዕቀብ ጥሎበት ነበር፡፡ ሻዕቢያ ግን ዓለም አቀፍ ዕውቅና የተቸረውን የያኔውን የሶማሊያን የሽግግር መንግስት ከአሸባሪው አል - ሸባብ ጋር አብሮ ለመጣል በማሴሩ እንዲሁም ራስ ዱሜራ በተሰኘው የጅቡቲ ግዛት በኃይል ያስገባቸው ወታደሮቹን ለማስወጣት ፈቃደኛ ባለመሆኑ የመጀመሪያውን ማዕቀብ እንደጣለበት ያስታውሳል–የፀጥታው ምክር ቤት።

ሃቁን ከአጣሪ ቡድኑ ሪፖርት በመነሳት ሲያጤነው፤ የአቶ ኢሳያስ መንግስት ነገር "ውኃ ቢወቅጡት እምቦጭ" እንዲሉት ዓይነት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ እንዲያውም ኬንያ በሚገኘው ኤምባሲው አማካኝነት እንደ ቋሚ ደመወዝተኛ በየወሩ 80 ሺህ ዶላር ሲሰጠው እንደነበር አጣሪ ቡድኑ አረጋግጧል። እናም በሁለተኛው ማዕቀቡ በአቶ ኢሳያስ ሹማምንቶች ላይ የጉዞ እና የኢኮኖሚ እንዲሁም የጦር መሣሪያ ዝውውር ዕገዳ ጥሎባቸዋል፡፡ ይህ ዕውነታም በሁለቱ ብ/ጄኔራሎች መሪነት የተካሄደው ምስጢራዊ ስብሰባ ላይ የተገለፀውና "...አል-ሸባብን ለሰባት ዓመት ተጠቅመንበታል" የሚለውን የመግለጫውን አካል ትክክለኛነት ብሎም የሻዕቢያን ማንነት ያጋለጠ ነው፡፡... "እውነት ብትቀጥንም አትበጠስም" ይሏል እንዲህ ነው።

ያም ሆነ ይህ እስቲ አሁን ደግሞ በሁለቱ ብ/ጄኔራሎች ስለተገለፀውና "የፈለግነውን ነገር ስላደረግን ከአሁን በኋላ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ጦርነት ማካሄድ አያዋጣንም፤ አያስፈልገንም" ወደሚለው ሁለተኛው ነጥብ ልውሰዳችሁ። ዕውን የኤርትራ መንግስት ከሀገራችን ጋር ጦርነት የማያደርገው የፈለገውን ነገር ስላደረገ ነውን?...የሃቁን መዝገብ አብረን እንግለጥ።...

እንደ እውነቱ ከሆነ የኤርትራ መንግስት ጦርነት ያለማድረግ ምክንያት ይህ አይደለም፡፡ ማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው፤ ላለፉት 21 ዓመታት እንደ ካሮት ቁልቁል ሲያድግ የነበረው የኤርትራ ኢኮኖሚ ላሽቋል። ከዚህ በተጨማሪም የሀገሪቱ ሠራዊት በየጊዜው ሥርዓቱን እየከዳ ወደ ጎረቤት ሀገሮች ከመሸሹም በላይ፣ የመዋጋት ሞራሉ ወድቋል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም። ዛሬ የኤርትራ ህዝብና ከ20 የማይበልጡ የሻዕቢያ ሹማምንቶች "ሆድና ጀርባ" ሆነዋል፡፡ አንዳንድ ለአስመራ ቅርበት ያላቸው ወገኖች እንደሚገልፁት ከሆነ፤ የሻዕቢያው አስተዳደር ኢኮኖሚውን መደጎም ስላልቻለ በእጁ የሚገኙትን መንግስታዊ አውታሮች ለመሸጥ

ውስጥ ውስጡን እየተደራደረ መሆኑ ይነገራል። ህዝቡም ቢሆን አቶ ኢሳያስን በማውገዝ የጥላቻ መፈክሮችን በየመንገዱ በመለጠፍ ላይ ይገኛል።

ታዲያ በእነዚህ ሁኔታዎች አጣብቂኝ ውስጥ የሚገኘው የኤርትራ መንግስት ምናልባት 'ትንኮሳ አካሂዳለሁ' አሊያም 'ወደ ሙሉ ጦርነት እገባለሁ' ብሎ ቢሞክር ምን ሊከተለው እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ይኸውም ያለው ኢኮኖሚ የሚያስበውን የጠብ አጫሪ ጦርነትን ሊሸከመው የማይችል፣ ሠራዊቱ የሀገሪቱ ጄኔራሎች እርሻ እንደ "ቀን ሰራተኛ" የሚያለማ በመሆኑ በማንኛውም ወቅት ሸርተት ሊል የሚችል እንዲሁም ለአንድ የጦርነት ድርጊት ወሳኝ የሆነው የህዝብ ድጋፍ ኤርትራ ውስጥ የነጠፈ በመሆኑ ትርፉ ራስን በራስ የማጥፋት ያህል ስለሚሆንበት ነው ፡፡ በመሆኑም በእኔ እምነት አቶ ኢሳያስና ጀሌዎቻቸው ወደ ጦርነት እንገባለን ቢሉ፤ በምላሹ የኢትዮጵያ መንግስት ለእያንዳንዱ ተግባራቸው ተመጣጣኝ እርምጃ ስለሚወሰድ በአንገታቸው ላይ ሸምቀቆ ማስገባት ስለሚሆንባቸው ፣ይህን ተግባር ይፈጽሙታል ተብሎ አይታሰብም፡፡

እናም ዕውነታው ይህ እንጂ፣ በምስጢራዊ ስብሰባው ላይ የተጠቀሰው ሻዕቢያ በሀገራችን ላይ "የፈለገውን ስላደረገ" አይደለም። ለነገሩ በአስመራው ቡድን ዘንድ ለራስ ሰው እንኳን ቢሆንም በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ ውሸትን ማውራት እንደ ትክክለኛ እሳቤ ስለሚቆጠር መግለጫ መሳዩ ዲስኩር የሚገርም አይደለም። ግና የብ/ጄኔራሎቹ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" ዓይነት የቅጥፈት መግለጫ ራስን በራስ በማፅናናት በፃዕረ-ሞት ላይ ያለን ማንነት ለማራዘም መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። እናንተዬ ማን ነበር "ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" ያለው?...መቼም የአስመራዎቹ የውሸት ቋቶች ሊሆኑ እንደማይቸሉ ተስፋ እናድርግ።...ቂ.ቂ.ቂ...

...እስቲ ለጥቀን ወደ ሶስተኛው አስገራሚ የአቶ ኢሳያስ በለሚሎች የጭንቀት ነጥብ እናምራ– "በሠራዊታችን ውስጥ ያለውን ማጉረምረምና ሃሜትን ፀጥ ለማሰኘት ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ የሆነ የሠራዊት አባላት ይቋቋማሉ። እነዚህ አባላትም ወደ ውጭ እንዳይኮበልሉ ከፍተኛ ቁጥጥር እናደርጋለን" ወደሚለው።... ለመሆኑ የኤርትራ ሰራዊት የሚያጉረመርመው ለምንድነው?፣ በላዩ ላይስ ፀጥ የሚያሰኘው ሌላ የስለላ ሰራዊት ለምን ይቋቋምበታል? –ምላሹን አብረን የምናየው ይሆናል።

ቀደም ሲል እንደገለፅኩት የኤርትራ ሰራዊት እዚህ ግባ የማይባል የመንግስት ናችፋ እየተከፈለው በተጨባጭ የሚሰራው ግን በጄኔራሎቹ የእርሻ ማሳ ውስጥ ነው። ከዚህ ባሻገርም ያለ አንዳች እረፍት በመንገድ ስራና ጠረጋ ላይ እንዲሰማራ ይደረጋል። አብዛኛዎቹ የሰራዊቱ አባላት ትምህርታቸውን አቋርጠው "ሳዋ" በተሰኘ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ በግዳጅ እንዲከትሙ የተደረጉ በመሆናቸው ሁሌም ደስተኞች አይደሉም። የአቶ ኢሳያስ ብሔራዊ ውትድርና

አገልግሎት መግቢያ እንጂ መውጫ ቀዳዳ የሌለው በመሆኑ በርካታ የሰራዊቱ አባላት ከማጉረምረም ባለፈ ወደ ጎረቤት ሀገሮች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይተምማሉ።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት የአቶ ኢሳያስን የግፍ አገዛዝ፣ እስርና እንግልት በመፍራትም በየወሩ በአማካይ 1 ሺህ 800 ኤርትራውያን የኢትዮጵያን ድንበር እያቋረጡ ይገባሉ። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ በአማካይ 45 በመቶ የሚሆኑት የኤርትራ መከላከያ ሠራዊት አባላት ሲሆኑ፤ አብዛኛዎቹም ወጣቶች ናቸው።

እናም በአሁኑ ወቅት እነዚህ የአቶ ኢሳያስ የሰራዊት አባላት ግፍና እንግልትን እየተቀበሉ በግድ ስርዓቱን አገልግሉ የሚባሉ በመሆናቸው መኩብለልን እንደ አማራጭ በመውሰድ ላይ ይገኛሉ። ይህም ለአቶ ኢሳያስና ለሹማምንቶቻቸው የራስ ምታት ሆኖባቸዋል። ለዚህም ነው ሁለቱ ብ/ጄኔራሎች አጠቃላይ የሰራዊቱን አባላት የሚሰልሉ ጥቂት አባላት እንደሚቋቋሙ በምስጢራዊው ስብሰባ ላይ የገለፁት። ይህ ዕውነታም የኤርትራ መከላከያ ሰራዊት ወታደራዊ ስነ-ልቦናዊ ዝግጁነቱ የሞተ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

የኤርትራ መንግስት ይቋቋማሉ ያላቸው ጥቂት የሰራዊት ሰላዮችም ቢሆኑ የሚታመኑ አይደሉም። ከመንግስቱ አምባገነናዊ ባህርይ በመነሳት እነርሱንም የሚቆጣጠር ሌሎች ሰላዮች አሉ– “በሰላይ ላይ ሰላይ” እንደማለት ነው። ግና በእንዲህ ዓይነት መንገድ ሀገርን ይጠብቃል የሚባል ሰራዊት ኤርትራ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር የትም የሚገኝ አይመስለኝም። ምክንያቱም “ሰራዊቴ በአጠቃላይ ሊከዳኝ ይችላል” በሚል ስሜት በሰራዊቱ ላይ ሰላይ፣ እንደገናም በሰላዮቹ ላይ ሰላይ መድቦ ሀገሩን የሚያስጠብቅ መንግስት ታይቶና ተሰምቶ ስለማይታወቅ ነው።

እርግጥ ይህ ሁኔታ የአስመራው ቡድን አሁን ያለበትን አጣብቂኝና ፍርሃት የሚያመላክት ከመሆን በዘለለ፤ፈላጭ ቆራጭ ስርዓቱ ቀስ በቀስ ለመውደቅ እየተንገታገተ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ግና ይህን መሰሉን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ እሳቤ ኤርትራ ያለውና በአስመራው አስተዳደር “ከፋፍለህ ምራው” አሰራር ውስጥ እየማቀቀ የሚገኘው  ሰራዊትም ሆነ ቤተሰቡ ምን እንደሚለው ባላውቅም፤ እኔ በበኩሌ ግን በአቶ ኢሳያስ የተላኩት ሁለቱ ብ/ጄኔራሎች የመሩትን ምስጢራዊ ስብሰባ መግለጫን ወንድም በሆኑት ኤርትራዊያን ስም “ደርግ ሲሄድ ሻዕቢያ ተተካ፣ ሐሰት አገላባጭ እውነትን ሳይነካ” የሚል ቅኔ ተቀኝቼለት ፅሑፌን ለመቋጨት ወደድኩ። ቸር እንሰንብት።